# ባለም ያወቀው እኛ ያላወቅነው

# የአንበሶቻችን ሚስጥር



ለዓመታት የቡና መገኛ በሆነችው የምዕራብ ኢትዮጵያዋ ከፋ አጉራባቿ አካባቢዎች ባሉ ዓለም ስትፈጠር ጀምሮ ተነክቶ የማያውቅ በሚመስለው ጥቅጥቅ ያለ ደን ውስጥ የሚገኘውን ወፍ ዘራሽ ቡና ለመልቀም ወደ ደኑ የሚዘልቁ የአካባቢው ነዋሪዎች በዚያ ዘወትር በጉም በተሸፈነ ደን ውስጥ ሰንሰለታማ ተራሮች እየተቀባበሉ እንደ ገደል ማሚቶ የሚያስተጋቡት ድምፅ የዚያ ባለአስፈሪ ግርማ የደኑ ንጉስ ድምፅ እንደሆነ ቢናገሩ ሰሚ ሳያገኙ ነው የኖሩት፡፡

‹‹በዚያ ከስድስት ወራት በላይ ዝናብ በማያጣ አካባቢ ባለ ደን ውስጥ ከመቼ ጀምሮ ነው አንበሳ ሊኖር የሚችለው? ዝም ብላችሁ በፍርሃት ትናጣላችሁ፡፡ አንበሳ እንዲህ ያለ ስፍራ ለመኖር አይችልም፡፡ ይህ ድምፅም የሌላ አውሬ ነው፡፡ እኛ አዲስ አበባ ያሉ አንበሶች ሲያገሱ እንሰማለን አይደለ?›› እያለ በአጋጣሚ ወደ ሥፍራው የሔደ አዲስ አበቤ ሳይቀር የአካባቢውን ነዋሪዎች እውነታ ያጣጥላል፡፡

ይህ ለዓመታት በአካባቢው ነዋሪዎች ይሠነዘር የነበረውን እውነታ ተቀባይነት አጥቶ የቆየው እስከ አለፈው ዓመት ድረስ ነበር፡፡ ያ አልፎ አልፎ በአስፈሪ ግርማ ሞገስ አካባቢውን የሚያደበላልቅ ድምፅ የምን እንደሆነ አይታወቅም ነበር፡፡ ጥቅጥቅ ባለው ደን አቅራቢያ የሠፈሩት የአካባቢው ነዋሪዎች ግን በቡድን በቡድን ሆነው የቡና ፍሬ ለቀማ በሚደርስ ጊዜ ወደ ደኑ ይዘልቃሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ታዲያ በተጠንቀቅ የሚሰሟት የማስጠንቀቂያ ወፍን ዝማሬ ከሠሙ የደኑ ንጉስ በአቅራቢያቸው እንዳለ በማወቅ ለቀማቸውን ትተው ወደ መንደራቸው ይመለሳሉ፡፡

ማንም የአካባቢው ነዋሪ የዚያችን የወፍ ድምፅ ሠምቶ ደኑ ውስጥ ለመቆየት አይፈቅድም፡፡ ብዙ ጊዜ ይህንን አቋማቸውን ይለውጡ ዘንድ ጥረት ቢደረግም አልተቀበሉትም፡፡ ‹‹በራሱ ግዛት ገብተን ብንበላ ማን ሊያድነን?›› ይላሉ፡፡

ተቀማጭነቱ በጀርመን ሀገር የሆነ ኔቸር ኤንድ ባዮዳይቨርሲቲ ኮንሰርቬሽን ዩኒየን (ናቡ) የተሰኘ በአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚሠራ ተቋም በአካባቢው የሚገኘውን 780 ስኩየር ኪሎ ሜትር ስፋት ያካለለ ደን በውስጡ የሚገኘውን ብዝሃ ሕይወትን ከጥቃት ለመጠበቅ የሚያስችሉ መረሃ ግብሮችን ነድፎ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋራ በመስራት ላይ ነው፡፡ የዚህ ፕሮጀክት ባልደረባ የሆኑ ተመራማሪዎች ነበሩ ለዓመታት በአካባቢው ነዋሪዎች ሲነገር የነበረውን በተራራማው የደን ክልል ውስጥ ምናልባትም ዝርያቸው በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኝ እንደሆነ የሚታመነው ባለጥቁር ጋማ ጉፈር ያለው አንበሳ በስፍራው እንደሚኖር ለማረጋገጥ የቻሉበት ዕድል አገኙ፡፡

በእርግጥም በአካባቢው Rare Ethiopian mountain Liones የሚል ስያሜ የተሰጣቸው በአለፉት ዓመታት በስድስት ኪሎ የአንበሳ ግቢ ውስጥ ከሚገኙት አንበሶች ላይ በተደረገ የዝርያ ጥናት የዲ.ኤን ኤ ምርመራ ባለ ጥቁር ጋማው የኢትዮጵያ አንበሳ በአፍሪካም ሆነ በተቀረው ዓለም ብዙ አንበሶች ዝርያ የተለየ የሰውነት መጠን የአካል ክፍል አወቃቀር እንዳለው በአይነቱ የተለየ ብቸኛ ዝርያ መሆኑን አረጋግጠው ነበር፡፡ ይህ በከፋ የቡና ደን ውስጥ ያለውም አንበሳ ዝርያ አንድ ዓይነት መሆኑን ተመራማሪዎች አረጋገጡ፡፡

ይህ ዜና በመላው ዓለም ያሉ የመስኩ ተመራማሪዎችን ያስደመመ ድንቅ ዜና ነበር፡፡ በአካባቢው የደን ሐብትና ብዝሃ ሕይወትን ከአደጋ ለመጠበቅ ከኢንተርናሽናል ክላይመንት ኤንሺቲቭ (አይ ኬ አይ) ከ 3-2 ሚሊዮን ዮሮ በላይ የገንዘብ ድጋፍ አደረገ፡፡ የጀርመኑ (ናቡ) ተቋም ይህንን በመጥፋት ላይ የሚገኝን የአንበሳ ዝርያን ለመታደግ ናቡ ላየን ፕሮቴክሺን ፕሮግራም የተሰኘ ፕሮግራም በመንደፍ ወዲያው ነበር ሥራውን የጀመረው፡፡

በአካባቢው ከ2009 እ.ኤ.አ ጀምሮ መንቀሳቀስ የጀመረው ይህ ተቋም በደኑ አካባቢ ከሚኖሩ ሕዝቦች ጋራ በተቀናጀ መልኩ ነው የአካባቢ ጥበቃውን የብዝሃ ሕይወት መንከባከቡን ሥራ የሚያከናውነው፡፡ ቀደም ባሉት ዓመታት በኢትዮጵያ ብቸኛው የእንስሳት ማሳያ ዙ አንበሳ ግቢ የሚገኙ አንበሶች የሚወልዷቸው ልጆች የመመገብ ዓቅም የላቸውም በሚል በመድኃኒት እንዲገደሉ ይደረግ የነበረው ተግባር መላውን ዓለም ያስደነገጠ ዜና ሆኖ ነበር፡፡

የተለያዩ የእንስሳት መብት ተከራካሪዎች፣ ተንከባካቢዎችና የኢትዮጵያ መንግሥት ባደረጉት ርብርብ አንበሶቹ ወደ ተለያዩ ቦታዎች እንዲወሰዱ በማድረግ ይህ አስደንጋጭ ተግባር እንዳይደገም አድረገዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የስድስት ኪሎ አንበሶች ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳት ማቆያ ሥፍራ ተገንብቶላቸው በቅርቡ ወደዚያ ይዘዋወራሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በከፋ ጥቅጥቅ ያለ ደን ተራራ አካባቢም እነዚህ ዝርያቸው አደጋ ላይ ነው፡፡ አንበሶቹ መኖራቸው ከተረጋገጠ በኋላ ከፕሬዝዳንቱ መኖሪያ ቤተ-መንግስትና ከስድስት ኪሎ አንበሳ ግቢ ታዳጊ አንበሶችን ወስዶ በደኑ ውስጥ በነፃነት እንዲኖሩ ተደርጓል፡፡

ናቡ የተባለው የጀርመን የአካባቢ ጥበቃ ተቋም በአካባቢው የሚታየውን የአንበሶችን ሕልውና ለመታደግና በአካባቢው ያሉ ነዋሪዎች አንበሶቹ ላይ ጥቃት እንዳይሠነዝሩ ለማድረግ በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ቁጥራቸው እንደጨመረ የሚታመነው በአካባቢ ጥቅጥቅ ያለ ደን ውስጥ የሚኖሩት አንበሶች በደኑ አቅራቢያ የሚኖሩ ነዋሪዎች ንብረት የሆኑ ከ 850 በላይ የቤት እንስሳትን መብላታቸው ሲታወቅ፤ ናቡ የተባው ተቋም ለቀንድ ከብቶቻቸው ለተበሉባቸው የአካባቢው ነዋሪዎች ተገቢውን ካሣ በመክፈል ነዋሪው በአንበሶቹ ላይ በበቀል ተነሳስቶ ጥቃት እንዲይሠነዝር የማድረግ ሥራ መስራቱ ታውቋል፡፡

ይህ የጀርመን የአካባቢ ጥበቃ ላይ የተሠማራ ተቋም በከፋ ጥቅጥቅ ያሉ ደኖች ውስጥ የሚኖረውን ዝርያው የተለየ ምናልባትም በዓለም ብቸኛው ባለጥቁር ጋማ አንበሳን አኗኗር አጠቃላይ ባህሪውን በተመለከተ አንድ “ኤክስፓንዴሺን ዘ ጃንግል ላየን” የተሰኘ ዘጋቢ ፊልም ለመስራት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

ይህ አንበሳ (በሣይንሳዊ ስሙ panthera leo) ወንዱ አንበሳ በአማካይ 189 ኪሎ ግራም ሲመዝን አልፎ አልፎ እስከ 260 ኪሎ የሚመዝን አንበሳ አለ፡፡ ሴትዋ አንበሳ ብዙ ጊዜ 126 ኪሎ ትመዝናለች፡፡ በአፍሪካ ውስጥ በ 26 ሀገራት የሚገኘው የአንበሳ ቁጥር ባለፉት አንድ መቶ ዓመታት በ85 ፐርሰንት ቀንሷል፡፡ በቅርቡ ይፋ የሆነ አንድ ጥናት እንደሚያመለክተው በኢትዮጵያ በሠባት ዋና ዋና አካባቢዎች ነው አንበሶች የሚገኙት፡፡ እነዚህ ስፍራዎችም

- ቦማ ጋምቤላ እስከ ደቡብ ሱዳን በሚዘልቅ በ106 941 ስኩየር ካሬ ሜትር ውስጥ ከ 500 በላይ አንበሳዎች
- በደቡብ ኦሞ በ22ሺህ 483 ስኩየር ካሬ ሜትር 200 አንበሶች
- በነጭ ሣር አካባቢ በ1ሺህ 030 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ውስጥ 10 አንበሶች
- በባሌ በ2ሺህ 373 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ውስጥ 50 አንበሶች
- በዋላማል ገናሌ በ6ሺህ 649 ስኩዌር ኪሎ ሜትር 100 አንበሶች
- በአዋሽ አካባቢ በ25ሺ 302 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ውስጥ 50 አንበሶች
- በኡጋዴን አካባቢ በ35ሺህ 405 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ውስጥ 100 ያቀፉ የአንበሳ ቤተሠቦች እንደሚገኙ ያሳያል፡፡

በኢትዮጵያ ያለው የአንበሳ ዝርያን በተመለከተ በተደረገ ጥናት ወንዱ አንበሳ ጋማው መታየት የሚጀምረው ሁለት ዓመት ከሞላው በኋላ ነው፡፡ ጋማው በጉልምስናው ትልቅ ይሆናል፡፡ እያረጀ ሲሄድ ደግሞ ይቀንሳል፡፡ አንበሶች ከሰው በቀር የሚፈሩት ፍጡር የለም፡፡

ከሃምሣ ዓመት በፊት በአዲስ አበባ የተቋቋመው በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አማካኝነት የተመሠረተው የአንባሳ ግቢ ያሉ ባለጥቁር ጋማ አንበሶች ዝርያ በዓለም አቀፍ ደረጃ መነጋገሪያ ሆኖ ብዙዎችን ሲያስደምም፤ እኛ አጠገባችን እያሉ ትኩረት ያልሰጠናቸው ለምንድን ነው? በካፋ ጫካ ውስጥ ለዓመታት ተከብረው በአካባቢው ነዋሪዎች ታውቀው፣ ተፈርተው ሲኖሩ የነበሩት አንበሶቻችን ሕልውና ለመጠበቅ ኔቸር ኤንድ ባዩዳይብርሲቲ ኮንሰርቬሺን ዮኒየን (ናቡ) በሥራ ላይ ያዋለው ፕሮጀክት ከሚመለከታቸው አካላት ሙሉ ድጋፍ እገዛ ሊደረግለት ይገባል፡፡ እኛሣ? እንደ ቀድሞው በአንበሳዎቻችን ብሔራዊ ምልክትነት የምንኮራ እንሆን ዘንድ ለተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ የበኩላችንን ግዳጅ እንወጣ፡፡ ከፈረንጆች ያልተሻለው ስለ ሀገራችን ያለን ዕውቀት እና ግንዛቢያችንንም እናስፋ፡፡ የፀሐፊው መልዕክት ነው፡፡